www.fag.gov.et

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ — ነሐሴ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1st Year No. 4
ADDIS ABABA 23rd August, 1995

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ ዓ.ም.
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ
አዋጅ ..... ገጽ ፵፫

CONTENTS

Proclamation No. 4/1995
Defination of Powers and Duties of the Excutive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation ..... Page 43

አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩ መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ «ክልል» ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል የሆነ ክልል ነው ።

PROCLAMATION NO. 4 / 1995

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE DEFINITION OF POWERS AND DUTIES OF THE EXECUTIVE ORGANS OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

WHEREAS, it is found necessary to define the powers and duties of the executive organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

NOW, THEREFORE. in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

PART ONE
General

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995."

2. Definition

In this Proclamation: "Region" means a Region specified under Article 47 of the constitution, being a member of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price } 3·60

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹፻፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

www.fag.gov.et

ክፍል ሁለት

ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩና ስለሚኒስትሮች ምክር ቤት

፫. ስለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፸፬ የተመለከተው ይሆናል ።

፬. ስለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣንና ተግባር በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፸፭ የተመለከተው ይሆናል ።

፭. ስለ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፸፯ የተመለከተው ይሆናል።

፮ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት

፩. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

ሀ. ጠቅላይ ሚኒስትር ፤
ለ. ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ፤
ሐ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ የተመለከቱትን ሚኒስትሮች የሚመሩ ሚኒስትሮች ፤
መ. ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአባልነት እንዲሳተፉ የሚመርጣቸው ሌሎች ባለሥልጣኖች ።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ) የተመለከተው ማንኛውም ሚኒስትር በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ የሚኒስትሩ ም/ሚኒስትር ወይም ከአንድ በላይ ምክትል ሚኒስትሮች ካሉ በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ሚኒስትር በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በምትክ አባልነት ይሳተፋል ።

፯. የሚኒስትሮች ምክር ቤት የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

፩. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ፤

ሀ. በውስጠ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ ያደርጋል፤
ለ. ምልአተ ጉባኤ የሚኖረው ከአባሎቹ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ይሆናል ፤
ሐ. የሚያስተላልፈው ውሣኔ በተባበረ ድምጽ ይሆናል ፣ በተባበረ ድምጽ መወሰን ካለተቻለ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል ፤
መ. የራሱ የውስጥ ደንብ ይኖረዋል ።

፪. ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፤

ሀ. የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይወስናል ፤
ለ. የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል ፤
ሐ. ለምክር ቤቱ በአጀንዳ የቀረበ ጉዳይ በምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ካገኘው ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ ያስተላልፋል ።

PART TWO

The Prime Minister, the Deputy Prime Minister and the Council of Ministers

3. *Powers and Duties of the Prime Minister*

The powers and duties of the Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall be as specified under Article 74 of the Constitution.

4. *Powers and Duties of the Deputy Prime Minister*

The powers and duties of the Deputy Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall be as specified under Article 75 of the Constitution.

5. *Powers and Duties of the Council of Ministers*

The powers and duties of the Council of Ministers of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shll be as specified under Article 77 of the Constitution.

6. *Members of the Council of Ministers*

1. The council of Ministers shall have the following members:

   a. the Prime Minister;
   b. the Deputy Prime Minister;
   c. Ministers that head the Ministries specified under Article 9 hereunder;
   d. other officials to be designated by the Prime Minister for participation in the capacity of membership.

2. Where any Minister referred to in Sub-Article (1) (c) of this Article cannot attend the meetings of the Council the Vice Minister or, in cases where there are more than one Vice Ministers, the Senior Vice Minster of the Ministry shall, take part in the meetings of the Council as a substitute member.

7. *Meeting Procedure of the Council of Ministers*

1. The Council of Ministers shall:

   a. hold ordinary and extraordinary meetings in accordance with its rules of procedure;
   b. have a quorum where more man half of its members are present;
   c. pass decisions by consensus or, failing that, by majority vote;
   d. have its own rules of procedure;

2. The Prime Minister shall:

   a. fix the agenda of the Council, without prejudice to the rights of the members of the Council of Ministers to propose an agenda;
   b. chair the meetings of the Council;
   c. postpone the meetings of the Council under circumstances where he finds it necessary to defer a case, brought before the Council itemized in its agenda, to a standing committee of the council;

www.fag.gov.et

፫· ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የምክር ቤቱን ስብሰባ ይመራል ።

3. In the absence of the Prime Minister, the Deputy Prime Minister shall chair the meetings of the council.

፰· የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች

8. Standing Committees of the Council

፩· የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባሩን ለመወጣት ይረዳው ዘንድ የምክር ቤቱ አባላት የሚገኙበት ልዩ ልዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ይኖሩታል ።

1. The council of Ministers shall, with a view to efficiently exercising its powers and duties, have various Standing Committees comprised of its members.

፪· የቋሚ ኮሚቴዎች ሥልጣንና ተግባር በምክር ቤቱ የውስጥ ደንብ ይወሰናል ።

2. The powers and duties of Standing Committees shall be defined in the rules of procedure of the council.

ክፍል ሦስት
ስለሚኒስቴሮች

PART THREE
Ministries

፱· የሚኒስቴሮች መቋቋም

9. Establishment

የሚከተሉት ሚኒስቴሮች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል ፤

The following Ministries are hereby established:

፩· የግብርና ሚኒስቴር
1. the Ministry of Agriculture;

፪· የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር
2. the Ministry of Economic Development and Cooperation;

፫· የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
3. the Ministry of Trade and Industry;

፬· የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር
4. the Ministry of Mines and Energy;

፭· የሥራና የከተማ ልማት ሚኒስቴር
5. the Ministry of Public Works and Urban Development;

፮· የውሃ ሀብት ሚኒስቴር
6. the Ministry of Water Resources;

፯· የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር
7. the Ministry of Transport and Communications;

፰· የጉንዘብ ሚኒስቴር
8. the Ministry of Labour and social affairs;

፱· የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
9. the Ministry of Finance;

፲· የትምህርት ሚኒስቴር
10. the ministry of Education;

፲፩· የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
11. the Ministry of Health;

፲፪· የፍትህ ሚኒስቴር
12. the Ministry of Justice;

፲፫· የማስታወቂያና የባህል ሚኒስቴር
13. the Ministry of Information and Culture;

፲፬· የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
14. the Ministry of Foreign Affairs;

፲፭· የአገር መከላከያ ሚኒስቴር
15. the Ministry of National Defence.

፲· የሚኒስቴሮች የወል ስልጣንና ተግባር

10. Common Powers and Duties of Ministries

እያንዳንዱ ሚኒስቴር፤

Each Ministry shall:

፩· በሥራው መስክ ፤
1. in its field of activity:

ሀ· ፖሊሲዎችንና ሕጐችን ያመነጫል ፣ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል ፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
a. initiate policies and laws, prepare plans and budget and, upon approval, implement same;

ለ· የፌዴራል መንግሥቱን ሕጐች ደንቦችና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል ፤
b. ensure the enforcement of laws, regulations and directives of the Federal Government;

ሐ· የጥናትና ምርምር ተግባር ያከናውናል ፣ የስታትስቲክስ መረጃዎች ይሰበስባል ፣ ያቀነባብራል ፤
c. undertake studies and research; collect and compile statistical data;

መ· ለክልል አስፈፃሚ አካላት እንዳስፈላጊነቱ ድጋፍና ምክር ይሰጣል ፤
d. give assistance and advice, as necessary, to Regional executive organs;

ሠ· በሕግ መሠረት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል ።
e. enter into contracts and international agreements in accordance with the law.

፪· በዚህ አዋጅ የተመለከቱትንና በሌሎች ሕጐች የተሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል ።
2. perform the duties specified in this Proclamation and such others as are assigned to it by other laws.

፫· ስለ ሥራው ክንዋኔ በየወቅቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል ።
3. Submit periodic activity reports to the Council of Ministers.

፲፩· የሚኒስትሮች ተጠሪነትና ኃላፊነት

11. Accountability and Responsibility of Ministers

፩· እያንዳንዱ ሚኒስትር የሚመራውን ሚኒስቴር ለሚመለከቱ ሥራዎች ፣ ፕሮግራሞችና ሕጐች አፈጻጸም ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሆናል ።
1. Each Minister shall, as regards the execution of responsibilities, programmes and laws concerning the given Ministry, be accountable to the Prime Minister and the Council of Ministers.

፪· እያንዳንዱ ሚኒስትር ፤
2. Each Minister shall:

ሀ· ሚኒስቴሩን ይመራል ይወክላል ፤
a. direct and represent the Ministry;

ለ· የሚኒስቴሩን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ያውላል፤
b. exercise the powers and duties of the Ministry;

www.fag.gov.et

ሐ· ለሚኒስቴሩ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል ።

፲፪· የግብርና ሚኒስቴር

የግብርና ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· የግብርና ልማት ኢንዲስፋፋ ያደርጋል ፤

፪· የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና የደንና ዱር አራዊት ጥበቃና አጠቃቀም ሕጐችን ያዘጋጃል ፤

፫· ለገበሬዎች የሚሰጡ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያበረታታል ፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

፬· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የግብርና ምርት ማሣደጊያዎች፣ የእርሻ መሣሪያዎች አገልግሎና የብድር አገልግሎቶች ለገበሬዎች የሚቀርቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፭· የግብርና ልማትን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጂን ለማሻሻል የሚረዱ የምርምርና የማሰልጠኛ ተቋሞችንና ማዕከሎችን ያቋቁማል ፣ ይመራል፤

፮· የሀገሪቱ የዕፅዋት ጄኔቲክ ሃብት እንዲጠናና እንዲጠበቅ ያደርጋል ፣ በሃገር ውስጥ የሚመረቱትንና ከውጭ እንዲገቡ የሚደረጉትን የተሻሻሉ ዘሮች የጥራት ደረጃ ይቆጣጠራል ፤

፯· የገበሬ ማኅበራት እንዲደራጁና የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲስፋፉ ያበረታታል ፤

፰· የግብርና ኢንቨስትመንትን ያበረታታል ፣ በግብርና ዘርፍ ለሚሰማሩ የውጭ ኢንቨስተሮች በግልጽ ለሌላ አካል በሕግ ከልተሰጠ በስተቀር የግብርና ሥራ ፈቃድ ይሰጣል ፣ ይቆጣጠራል ፤

፱· ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከሃገር በሚወጡ ዕፅዋት ፣ አዝርዕት እንስሳትና የእንስሳት ተዋፅኦ ላይ ተገቢው የኳራንቲን ቁጥጥር እንዲካሄድ ያደርጋል ፤

፲· በሃገሪቱ ውስጥ በጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የእንስሳት መድሃኒትና ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል ፤

፲፩ በእንስሳት ርቢ ላይ ለተሠማሩ ህዝቦች አስፈላጊው የኤክስቴንሽን ድጋፍ እንዲሰጥ ያደርጋል ።

፲፫· የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር

የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩· የሃገሪቱን የረጅም ጊዜ የልማት አቅጣጫ ለመተለምና በዚሁ ላይ ተመሥርቶ የልማት ቅደም ተከተልና ስትራቴጂ ለመቀየስ የሚያስችሉ የፖሊሲ ሐሳቦችን ያመነጫል፤

፪· በሃገሪቱ የልማት ስትራቴጂ ላይ የተመሠረተና በፌዴራል መንግሥቱ የሚፈጸም የረጅም ፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል ፤

፫· የአገሪቱን የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ያዘጋጃል ፣ ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፬· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በረጅም፣ በመካከለኛና በአጭር ጊዜ ዕቅዶች ውስጥ የሚንፀባረቁ በፌዴራል መንግሥቱ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች እንዲጠኑና እንዲዘጋጁ ያደርጋል ፣ ይገመግማል ፤

፭· በፌዴራል መንግሥቱ አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርቡ ለትን ዓመታዊ የልማት ዕቅዶች ለእነዚህም የሚያስፈልጉ የካፒታል በጀት ጥያቄዎች መርምሮ የልማት ዕቅድና ካፒታል በጀት ካዘጋጀ በኋላ ከፌዴራል መንግሥቱ ዓመታዊ ጠቅላላ በጀት ጋር ተዋሕዶ እንዲዘጋጅ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያስተላልፋል ፣ ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይከታተላል ፤

c. effect expenditure in accordance with the budget approved for the Ministry.

12. The Ministry of Agriculture

The Ministry of Agriculture shall have the powers and duties to:

1. cause the expansion of agricultural development;
2. prepare land-use policy as well as draft laws on the conservation and utilization of forest and wildlife resources;
3. encourage and assist the provisions of agricultural extension services to peasants;
4. facilitate the provisions of agricultural inputs, agricultural mechanization services and credit facilities to peasants;
5. establish and direct research and training establishments that may assist the enhancement of the development of agriculture and the improvement of rural technology;
6. cause the undertaking of studies pertaining to and the protection of the country's plant genetic resources; control the quality of improved seeds produced locally or imported;
7. encourage the organization of peasants and the development of peasant cooperatives;
8. encourage agricultural investments; except insofar as such power is expressly given by law to another organ, issue agricultural licences to and supervise foreign investors engaged in agricultural activities;
9. ensure the conducting of quarantine controls on plants, seeds, animals and animal products brought into or taken out of the country.
10. register and control veterinary drugs and pesticides to be used in the country;
11. cause the provision of assistance in necessary extension services to pastoralist peoples.

13. The Ministry of Economic Development and Cooperation

The Ministry of Economic Development and Cooperation shall have the powers and duties to:

1. Initiate policy proposals that help to define the country's long-term development perspective and, on the basis of same, to set development priorities and strategy;
2. prepare and, upon approval, follow up the implementation of long, medium and short – term development plans that are based on the country's development strategy and to be executed by the Federal Government;
3. prepare the population policy of the country; and, upon approval, follow up its execution;
4. in cooperation with the concerned organs, cause the study and preparation of and review projects based on the long, medium and short-term plans and to be executed by the Federal Government;
5. prepare annual development programme and supporting capital budget proposal upon analyzing development programmes and supporting capital budget proposals received from Federal Government organs; present said annual development programme and supporting capital budget proposal to the Ministry of Finance for consolidation into the annual Federal Government budget and, upon approval, follow up the implementation of same;

www.fag.gov.et

፮· የግሉ ክፍለ ኤኮኖሚ በአመልካች ፕላን እየታገዘ የኢንቨስትመንት ውሣኔ ለማድረግ የሚችልባቸውን የሥራ መስኮች ይጠቁማል ፣ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የግሉን ዘርፍ ለማበረታታትና ለማሳደግ የሚረዱ የፖሊሲ ሐሳቦችን ያመነጫል ፤

፯· የሀገሪቱን የረጅም ፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት ዕቅድ ለማዘጋጀት የሚረዳ የኢኮኖሚ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል ፣ የፕላን ሜቶዶሎጂና አጠቃላይ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሁኔታ መለኪያዎችንና መመዘኛዎችን ያዘጋጃል ፤

፰· በሥራው መስክ የካርታ ፣ የስታቲስቲክስና ሌሎች የልማት መረጃዎች ሥራ እንዲከናወኑ ያደርጋል ፤

፱· የፕላን አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያዎችን ያወጣል፣ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲ ደርሱ ያደርጋል ፤

፲· የውጭ የልማት ዕርዳታና ብድር በዓይነትና በመጠን እንዲጨምር ልዩ ልዩ ስልቶችን ይቀይሳል፣ የዕርዳታና የብድር ስምምነቶችን ይደራደራል ፣ ይፈርማል ፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፣

፲፩· የልማት ዕቅዶችን አፈጻጸም እየገመገመ ዓመታዊ ሪፖርት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል ።

፲፬· <u>የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር</u>

የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩· ንግድ ኢንዱስትሪና ዕደ ጥበብ እንዲስፋፋ ያደርጋል ፤ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች በንግድና ኢንዱስትሪ ስራ ላይ በሰፊው እንዲሰማሩ ያበረታታል ፤ የቴክኒክ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶችን ይሰጣል ፤

፪· በኢንቨስትመንት ፖሊሲና ህግ መሠረት የፌዴራሉ መንግሥት ሊሠማራባቸው የሚችሉ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ያመነጫል ፤ እንዲጠኑና ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል ፤

፫· ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ሥራዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

፬· የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን እያጠና ያቀርባል ፤ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

፭· በክልሎች መካከል የሚደረግን የንግድ ግንኙነትና የውጭ ንግድን ይመራል፣ ይቆጣጠራል ፤

፮· የሃገሪቱ የኢንዱስትሪ ፣ የእርሻና ሌሎች ውጤቶች በሃገር ውስጥና በውጭ እንዲታወቁ ያደርጋል፣ በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ኤግዚቢሽን እንዲዘጋጅ ያደርጋል ፤ በሌሎች አገሮች ኤግዚቢሽን ላይ ይሳተፋል፤

፯· በውጭ ንግድ ሥራ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች እንዲሁም በማናቸውም የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ሥራ ለሚሰማሩ የውጭ ባለሀብቶች ሥልጣኑ በግልጽ ለሌላ አካል በህግ ካልተሰጠ በስተቀር ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

፰· ማዕከላዊ የንግድ መዝገብ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

፱· የንግድ ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ ያበረታታል ፤ በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚቋቋሙ የንግድ ምክር ቤቶች ድጋፍ ይሰጣል ።

፲፭· <u>የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር</u>

የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል

6. identify investment areas on indicative plans to assist the private sector in making investment decisions; in cooperation with the appropriate organs, initiate policy proposals with a view to encouraging and promoting the private sector;
7. undertake economic studies and research and prepare plan methodology and general macro-economic and social parameters and guidelines that enable the preparation of the country's long, medium and short-term development plans;
8. cause the carrying out in mapping, statistical and other development information, in its own field;
9. prepare plan preparation and presentation guidelines; ensure the distribution in due time of same to concerned organs;
10. formulate strategies with a view to increasing the type and volume of foreign development aid and loans; negotiate and sign aid and loan agreements and, in cooperation with the concerned organs, follow up their implementaition;
11. evaluate the execution of development plans and submit annual report to the Council of Minisiers.

14. *The Ministry of Trade and Industry*

The Ministry of Trade and Industry shall have the powers and duties to:

1. cause the expansion of trade, industry and handicrafts; encourage the extensive engagement of domestic investors in trade and industrial activities; provide technical, advisory and other services;
2. initiate industrial projects in which the Federal Government may engage itself in accordance with the investment policy and law; cause same to be studied and implemented;
3. conduct studies that help to control unfair trade practices, and follow up their implementation;
4. undertake studies relating to basic commodities and services that have to be under price-control and upon approval, follow up the implementation of same;
5. direct and control trade carried out amongst Regions as well as foreign trade;
6. cause the organization of exhibitions, within the country and in other countries, of the Country's industrial, agricultural and other products and participate in exhibitions organized by other countries;
7. except insofar as such power is expressly given by law to another organ, issue licences to and supervise investors engaged in foreign trade as well as foreign investors engaged in any trade or industrial activity;
8. organize and administer a central commercial register;
9. encourage the establishment of chamber of commerce; give assistance to the chamber of commerce established at the national level.

15. *The Ministry of Mines and Energy*

The Ministry of Mines and Energy shall have the powers and duties to:

www.fag.gov.et

፩· የሃገሪቱ የማዕድንና ኢነርጂ ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

፪· የማዕድንና የኢነርጂ መረጃዎችን ይሰበስባል ፣ በሚገባ እንዲያዙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፣ ዘገባዎችን ያዘጋጃል፣ ያሠራጫል፤

፫· ስለ ማዕድን ሃብት ጥበቃና አጠቃቀም ሕግ ያዘጋጃል፤

፬· በማዕድን ፍለጋና ልማት ለሚሠማሩ የግል ኢንቨስ ተሮች በሕግ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል ።

፭· ስለ ኢነርጂ ልማትና አጠቃቀም ጥናት ያካሂዳል ፣ የሃገሪቱ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እንዲያድግና እንዲስፋፋ ያደርጋል ፤

፮· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለሃገሪቱ የሚያስፈልገው ጋዝ ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች እንዲ ቀርቡ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

፯· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢነርጂ መጠባበቂያ ክምችት መጠንን ይወስናል ፣ ክምችቱ እንዲኖር መደረጉን ያረጋግጣል፤

፰· የማዕድንና የኢነርጂ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ የምርምርና የማሰልጠኛ ተቋሞችን እንዳስፈላጊነቱ ያቋቁማል ።

፲፮· <u>የሥራና የከተማ ልማት ሚኒስቴር</u>

የሥራና የከተማ ልማት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩· የሀገሪቱን የሕንጻ ኮድ ያዘጋጃል ፣ ለዲዛይንና ለኮንስት ራክሽን ሥራዎች ደረጃ ያወጣል ፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፪· በፌዴራል መንግሥት በጀት ለሚሠሩ የመንግሥት ኮንስትራክሽኖች የሚያስፈልጉ ዲዛይኖችና የኮንስትራ ክሽን ሥራ ውሎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል ፤

፫· በፌዴራል መንግሥቱ የሚከናወን የመንግሥት ኮንስ ትራክሽን በተገባለት ውል መሠረት የጥራት ደረጃው ፣ የጊዜና የዋጋ ገደቦች ተጠብቀው መሠራቱን ለማረ ጋገጥ የሚያስችል ቁጥጥር እንዲኖር ያደርጋል ፣ በበላ ይነት ይቆጣጠራል፤

፬· በፌዴራል መንግሥትም ሆነ በክልል በጀት የሚከ ናወን የመንግሥት ኮንስትራክሽንን በሚመለከት የዲዛይን ፣ የኮንስትራክሽንና የቁጥጥር ሥራዎች በዓለም አቀፍ ጨረታ ለውጭ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች የሚሰጡበትን ሁኔታ ይወስናል ፤

፭· መሐንዲሶችንና አርክቴክቶችን ይመዘግባል፣ የሙያ ችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የሥራ ተቋራጮችንና የአማካሪዎችን ደረጃ ይወስናል፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ተወዳድረው መሥራት ለሚችሉ የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች እንዲሁም በውጭ ባለሀብቶች ለሚቋቋሙ የሥራ ተቋራጭና የአማካሪ ድርጅቶች ፈቃድ ይሰጣል ፣ ይቆጣጠራል፤

፮· በአገር ውስጥ የሚመረቱ የኮንስትራክሽን ዕቃዎችን ዓይነትና ጥራት ለማሻሻል የሚረዳ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤

፯· አከታተምን በሚመለከት ጥናት ያካሂዳል ፣ የከተሞችን ደረጃ መመዘኛ ያወጣል ፣ ከክልሎች በሚቀርብለት ጥያቄና በሚያወጣው ቅደም ተከተል መሠረት የከተሞች ማኅበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ሁኔታዎች ተጠንተው መሪ ፕላኖች እንዲዘጋጅላቸው ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸውን በሚመለከት ለክልል መስተዳድሮች የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል ፤

፰· ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ የመንግሥት አካል በሕግ ካልተሰጠ በስተቀር በፌዴራሉ መንግሥት ባለቤትነት ሥር የሚገኙ የከተማ ቤቶችን በበላይነት ያስተዳ ድራል፣ እንዲታደሱና እንዲጠገኑ ያደርጋል ፤

1. cause the expansion of the mines and energy development of the country;
2. collect and maintain a depository of mineral and energy data and prepare reports;
3. prepare draft laws on the conservation and utilization of mineral resources;
4. license and supervise, in accordance with the law private investors to be engaged in the prospecting & mining of minerals;
5. undertake studies concerning the deveopment and utilization of energy; and promote the growth and expansion of the country's electric energy supply;
6. in cooperation with the appropriate organs, ensure the availability of gas, petroleum and by-products necessary for the country;
7. in cooperation with the appropriate organs, determine the volume of energy reserves and ensure that same is maintained;
8. establish, as may be necessary, research and training centers that may asist the enhancement of the development of mining and energy.

16. The Ministry of Public Works and Urban Development

The Ministry of Public Works and Urban Development shall have the powers and duties to:

1. prepare the country's building code; issue standards for design and construction works; and follow up and supervise the implementation of same;
2. cause the preparation of designs and contract documents necessary for government construction financed by the Federal Government;
3. cause the supervision of and inspect, the execution of construction works financed by the federal Government to ensure their conformity with the quality standards, time limits and cost as provided in their contracts;
4. determine conditions under which design, construction and supervision contracts concerning construction works financed by the Federal Government or the Regional Governments may be awarded to foreign contractors and consultants;
5. register and issue certificates of competence to engineers and architects; determine the grade of contractors and consultants; license and supervise local contractors and consultants that may be able to compete at the national level as well as construction and consulting firms established by foreign investors;
6. undertake study and research activities with a view to improving the types and qualities of local construction materials;
7. undertake studies relating to urbanization patterns; prescribe standards for the grading of urban centers; upon the request of Regional Governments and in accordance with priorities set by it, cause studies to be undertaken pertaining to the social, economic and other factors of urban centers and the preparation of master plans for them, and provide technical assistance to Regional Governments with regard to the implementation of same;
8. supervise the administration of urban houses owned by the Federal Government except insofar as such power is specifically given by law to another government organ, and cause the repair and maintenance of same;

www.fag.gov.et

፱. የከተማ ነዋሪው ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠኑ መኖሪያ ቤቶችን ሠርቶ እንዲጠቀም ሁኔታዎችን እንዲመቻቹ ያደርጋል ፤

፲. የመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል ፣ ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ይቀይሳል፤

፲፩. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለኮንስትራክሽንና ለከተማ ልማት ዘርፍ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል እንዲሰለጥን ያደርጋል ፣ እንዳስፈላጊነቱም የማሠልጠኛ ተቋሞችን ያቋቁማል ፤

፲፪. ለሥራው ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣኑ በከፊል ለሌላ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት በውክልና ይሰጣል ።

፲፯. የውሃ ሃብት ሚኒስቴር

የውሃ ሀብት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩. ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን አቋርጦ የሚፈስ ወይም የሚያዋስን ውሃ በልዩ ልዩ የግልጋሎት ዓይነቶችና በክልሎች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈል በትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታና ዘዴ ይወስናል፤

፪. ስለውሃ ሃብት ጥበቃና አጠቃቀም ሕጐች ያዘጋጃል፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) በተጠቀሱት ውሃዎች ላይ የውሃ ሥራዎች ለመስራትና በጥቅም ላይ ለማዋል ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል ፤

፬. ስለ ውሃ ታሪፍ ፖሊሲ ተገቢውን ጥናት ያደርጋል ፣ ሲፈቀድም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሱትን በሚመለከት የውሃ ጅምላ ክፍያ ያስከፍላል ፣

፭. ስለ ወሰን ተሻጋሪ ወንዞች አጠቃቀም ጥናቶች ያደርጋል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

፮. የውሃ ሀብት በአግባቡ ለልማት ስራ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችሉ ዕቅዶችን ያዘጋጃል ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይቆጣጠራል ፤

፯. የውሃ ሃብት ልማትን በተመለከተ አስፈላጊ ሆነው የተገኙትን ድጋፎች ሁሉ ይሰጣል ፤

፰. ወሰን ተሻጋሪ ወንዞችን በተመለከተ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በሕግ መሰረት ይፈርማል ፤

፱. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለልዩ ልዩ ግልጋሎቶች የሚውል ውሃ ሊይዝ የሚገባውን የጥራት ደረጃ ይወስናል ፤

፲. የሜትሮዎሎጂ አገልግሎት በሚገባ መካሄዱን ይቆጣጠራል ።

፲፰. የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩. የአየር ፣ የባቡርና የባህር መጓጓዣ፣ እንዲሁም የፖስታና የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል ፣ ይቆጣጠራል ፤

፪ የትራንስፖርትና የመገናኛ አገልግሎቶችን ለመቆጣጠር የሚረዱ ሕጐችን ያዘጋጃል ፤

፫. የሀገሪቱ የትራንስፖርትና የመገናኛ ዓይነቶች ተደጋግፈው የሚያድጉበትንና በተቀነባበረ ሁኔታና በሚገባ በጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል ፤

፬. የባህርና የትራንዚት አገልግሎት እንዲሁም ክልሎችን የሚያገናኙ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎቶችን ይቆጣጠራል፤

9. ensure the provision of facilities to urban dwellers so that they may be able to construct and use dwelling houses compatible with their own means;

10. encourage the establishment of housing cooperatives, and devise ways and means for providing assistance to them;

11. in cooperation with the appropriate organs, cause the training of manpower necessary for the construction and the urban development sector; and establish training institutions as may be necessary;

12. delegate part of its powers to another Federal Governmet organ when it deems it necessary for purposes of efficiency.

17. *The Ministry of Water Resources*

The Ministry of Water Resources shall have the powers and duties to:

1. determine conditions and methods required for the optimum allocation and utilization of water that flows across or lies between more than one Regional Governments among various uses and regions;
2. prepare draft laws concerning the protection and utilization of water resources;
3. issue permits to construct and operate water works relating to waters referred to in ub-article (1) of this Article; and regulate same;
4. make appropriate studies concerning water tariff and, upon approval, collect bulk charges for water use under sub-article (1) of this Article;
5. undertake studies pertaining to the utilization of the waters of transboundary rivers and, upon approval, follow up the implementation of same;
6. prepare plans that help to properly utilize water resources for development purposes supervise their implementation upon approval;
7. provide all the assistance deemed necessary with regard to water resources development;
8. sign international agreements relating to transboundary rivers, in accordance with the law;
9. in cooperation with the appropriate organs, prescribe the quality standards for waters to be used for various purposes;
10. supervise the proper rendering of meteorological services.

18. *Ministry of Transport and Communications*

The Ministry of Transport and Communications shall have the powers and duties to:

1. cause the expansion of, and supervise, air, rail and sea transport services as well as postal and telecommunications services;
2. prepare draft laws concerning the regulation of transport and communications services;
3. facilitate the integrated development and effective and coordinated utilization of all modes of transport and communication of the country;
4. regulate maritime and transit services as well as road transport services that link Regions;

www.fag.gov.et

፭· የአየር ፣ የየብስ፣ የባቡርና የባህር መጓጓዣዎችንና የመገናኛ አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎችን ስለመመዝገብ በነዚሁ ላይ ስለሚደረግ የቴክኒክ ምርመራና ስለሥራና መንጃ ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ያወጣል ፣

፮· ማናቸውንም የኢትዮጵያ መርከብ ይመዘግባል ፣ ለባሕር ጉዞ ብቁነቱ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፯· የአየር ወይም የባሕር ማመላለሻ አደጋ በደረሰ ጊዜ የፍለጋና የማዳን ተግባር እንዲካሄድና ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፰· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለትራንስፖርትና መገናኛ ዘርፍ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል እንዲሰለጥን ያደርጋል ።

፲፱· <u>የገንዘብ ሚኒስቴር</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩· በፌዴራል መንግሥቱ አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርቡ ለትን የመደበኛ በጀት ጥያቄዎች ፣ በኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የሚተላለፍለትን የካፒታል በጀት እና በክልሎች የሚቀርብለትን የበጀት ድጎማ ጥያቄዎች መርምሮ የፌዴራል መንግሥቱን የተጠቃለለ ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ከአስተያየቱ ጋር ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል ፣ የተፈቀደውን በጀት ያስተዳድራል ፤

፪· የፌዴራል መንግሥቱን የፋይናንስ ክንውንና የገንዘብ ይዞታ የሚያሣይ ጠቅላላ መግለጫ በየወቅቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል ፣ አስፈላጊ ሲሆንም ተጨማሪ በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል ፤

፫· የፌዴራል መንግሥቱን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ይመሠርታል ፤ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል ፣ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሂሣብ እንዲሁም የፌዴራል መንግሥቱ ለክልሎች የሚሰጠውን የበጀት ድጎማ ሂሣብ ይመረምራል ፤

፬· አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከሀገር ውስጥ የብድር ምንጮች በፌዴራል መንግሥቱ ስም ይበደራል ፣ ከሃገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚገኙ የፌዴራል መንግሥቱን ብድሮች ያስተዳድራል ፤

፭· የፌዴራል መንግሥቱን አክሲዮኖች ፣ የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችና ሌሎች ተመሣሣይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል ፣ ይጠብቃል ፤

፮· ለልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥቱ ዕቃዎች ግዥና አጠቃቀም መመሪያ ያወጣል ፣ ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል ፣ ለክልል መስተዳድሮች የዕቃ ግዥና አጠቃቀም መመሪያ አዘገጃጀት ድጋፍ ይሰጣል፤

፯· በሌላ የፌዴራሉ መንግሥት አካል ሥር የማይተዳደር ወይም ጥቅም ላይ ያልዋለ የፌዴራል መንግሥቱ ንብረት ኃላፊ ሆኖ ያስተዳድራል ፤

፰· ከብሔራዊ ባንክና ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት ፣ መረጋጋትና ፍትሃዊነት አንዲሁም ጤናማ የገንዘብ ልውውጥና ተመን ለማምጣት ትክክለኛ የሞኒተሪ ፖሊሲ ያመነጫል ፤

፱· የፌዴራል መንግሥቱን ዓመታዊ የፋይናንስ ክንውንና ስለመንግስት ጠቅላላ ገቢና ወጪ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል ።

፳· <u>የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር</u>

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

5. issue directives concerning the registration and inspection of air, land, rail and sea carriers and communications equipment, the granting of operating permits and the licensing of operators;
6. register all Ethiopian ships; issue certificates on their sea worthiness;
7. provide for search and rescue operations and for the taking of appropriate measures in the case of air or marine transport accidents;
8. in cooperation with the appropriate organs, cause the training of manpower necessary for transport and communications sector.

19. *The Ministry of Finance*

The Ministry of finance shall have the powers and duties to:

1. prepare and submit to the Council of Ministers, together with its recommendations, a consolidated annual budget of the Federal Government upon analyzing recurrent budget proposals received from Federal Government organs, capital budget proposals prepared and forwarded to it by the Ministry of Economic Development and Cooperation and requests from Regional Governments for budgetary subsidies; and administer the approved budget;
2. submit periodically to the Council of Ministers general report on the Federal Government's financial operation and situation; prepare and submit supplementary budget when necessary;
3. establish accounting systems for the Federal Government and supervise the implementation of same; inspect the accounts of Federal Government organs and the accounts of Regional Governments with respect to budgetary subsidies granted to them by the Federal Government;
4. borrow money in the name of the Federal Government from internal sources in accordance with the appropriate law; administer the Federal Government's internal and external debts;
5. be the repository of and safeguard the Federal Government's shares, negotiable and non-negotiable instruments and other similar financial assets;
6. issue and supervise the implementation of directive concerning the purchase and utilization of Federal Government supplies; assist in the preparation of directives concerning the purchase and utilization of Regional Governments' supplies;
7. account for and administer property of the Federal Government which is not administered or used by any other organ of the Federal Government;
8. in cooperation with the National Bank and other concerned organs, initiate proper monetary policy with a view to enhancing the country's economic growth, stability and justice as well as the normalization of money circulation and exchange rates;
9. submit to the Council of Ministers reports on the annual financial operation of the Federal Government and on total Government revenue and expenditure.

20. *The Ministry of Labour and Social Affairs*

The Ministry of Labour and Social Affairs shall have the powers and duties to;

www.fag.gov.et

፩· አሠሪና ሠራተኛን የሚመለከቱ ሕጐች ያዘጋጃል ፣ ሲፀድቁም በሥራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል ፤

፪· የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የሚያስ ፈልጉ የሥራ ሁኔታ ፣ ደረጃዎችንና የመከላከያ ዘዴዎችን ይወስናል ፤ ተግባራዊነታቸውን ይከታ ተላል፤

፫· ስለ ሠራተኛና አሠሪ ማህበራት ምዝገባ መመሪያ ያወጣል ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደራጁትን የሠራ ተኛና የአሠሪ ማህበራት ይመዘግባል ፣ ድጋፍ ይሰጣል ፤

፬· የህብረት ስምምነት ድርድሮችና የሥራ ክርክሮች በሕግ የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትለው በተቀላጠፈ ሁኔታ ፍጻሜ የሚያገኙበትን መንገድ ይቀይሳል ፣ ድጋፍ ይሰጣል ፤

፭· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በአገሪቱ ውስጥ በሥራ ላይ ስለተሰማራው የሰው ኃይልና ስለ ሙያ አመዳደብ ጥናት ያደርጋል ፤

፮· ሥራ ፈላጊዎችና ክፍት የሥራ መደቦች ስለሚመዘገ ቡበት ፣ ሥራና ሠራተኛ ስለሚገናኙበት መንገድ መመሪያ ያወጣል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ለውጭ ዜጐችና ዜግነት ለሌላቸው ሰዎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ይወስናል፣ ፈቃድ ይሰጣል፤

፯· ስለ ሰው ኃይልና የሥራ ሥምሪት ፣ ስለሠራተኞች ደህንነትና ጤና እንዲሁም አሠሪና ሠራተኛን ስለሚመ ለከቱ ሌሎች ጉዳዮች መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠና ቅራል ፣ ያሠራጫል፤

፰· ሴቶች በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚ ፣ በማህበራዊና በባህል መስኮች ከወንዶች ጋር በእኩልነት እንዲሳተፉ በተለይ በትምህርት ፣ በሥልጠናና በሥራ ከመንግሥት ልዩ ድጋፍ ስለሚያገኙበት ሁኔታ ያጠናል ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፱· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ሕጻናትና ወጣቶች መልካም አስተዳደግ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያጠናል ፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፍ ይሰጣል ፤

፲· አረጋውያንና የአካል ጉዳተኞች የሚረዱበትን እንዲሁም አካል ጉዳተኞችን መልሶ ለማቋቋም የሚያ ስችሉ ዘዴዎችን ያጠናል ፣ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል ፤

፲፩· የማሕበራዊ ኑሮ ጠንቆች የሚወገዱበትን መንገድ ያጠናል፣ ጠንቆቹን በማስወገድ ረገድ አግባብ ያላቸውን አካላት ያስተባብራል፣ አስፈላጊውንም ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፪· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የቤተሰብ ደህንነት ስለሚጠበቅበትና ለጋብቻ ሥርዓት ስለሚ ደረግ እንክብካቤ ጥናት ያካሂዳል ፣ ሲፈቀድም ተግባራ ዊነቱን ይከታተላል ፤

1. prepare draft laws concerning labour relations and, upon approval, supervise their enforcement;
2. determine standards and measures for the safety and health of workers and follow up their implementation;
3. issue directives concerning the registration of employers' and workers' unions register and assist employers' and workers' unions established at the national level;
4. facilitate and assist the efficient settlement of collective bargaining and labour disputes following the prescribed legal procedure;
5. in cooperation with the appropriate organs, undertake studies on the manpower employed in the country and on occupational classification;
6. issue and follow up the implementation of directives regarding the registration of job-seekers and vacancies and employment exchnge; determine conditions for the issuance of, and issue, work permits to foreign nationals and stateless persons;
7. collect, compile and disseminate information on manpower and employment, safety and health of workers and on other matters relating to labour relations;
8. undertake studies regarding special government assistance to be given to women, in particular in the field of education, training and employment, so that they should be able to have equal participation with men in political, economic, social and cultural activities; and follow up the implementation of same upon approval;
9. in cooperation with the appropriate organs, study, and give assistance for, the implementation of ways and means for the proper upbringing of children and youth;
10. study and, in cooperation with the appropriate organs, ensure the implementation of ways and means for providing assistance to the aged and the disabled as well as the rehabilitation of the disabled;
11. undertake studies on the prevention of social problems; coordinate and give assistance to the appropriate organs in eliminating social problems;
12. in cooperation with the appropriate organs, study and, upon approval, follow up the implementation of ways and means for the protection of family and marriage institutions.

፳፩· <u>የትምህርት ሚኒስቴር</u>

የትምህርት ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· ትምህርትን በአገር አቀፍ ደረጃ ለማስፋፋት የሚያ ስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል ፣ ለተግባራዊነታቸውም ሁኔታዎችን ያመቻቻል ፤

፪· በአገር አቀፍ ደረጃ ሊኖር የሚገባውን የትምህርት ስታንዳርድ ይወስናል ፣ ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣ ጠራል ፤

21. The Ministry of Education

The Ministry of Education shall have the powers and duties to:

1. devise and facilitate the implementation of ways and means of extending education throughout the country;
2. determine and supervise the implementation of the country's educational standard;

www.fag.gov.et

፫· በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋሞችና በተመሣሣይ ደረጃ በሚገኙ የሙያ ማሰልጠኛ ተቋሞች የሚሰጠውን ሥርዓተ ትምህርትና ለተማሪዎች የሚሰጡትን የምስክር ወረቀቶች ዓይነትና ደረጃ ይወስናል ፣ በክልል ደረጃ ለሚከናወን የአንደኛና የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ድጋፍ ይሰጣል ፣ በማናቸውም ደረጃ የሚዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት ከሃይማኖትና ከፖለቲካ አመለካከት ፣ ከባህላዊ ተጽዕኖዎች ነጻ መሆኑን ያረጋግጣል ፤

፬· በየደረጃው ለማስተማር ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎችን ያወጣል ፣ እንደአስፈላጊነቱ መምህራንንና የትምህርት ባለሙያዎችን ያሰለጥናል ፣ በክልል ደረጃ ለሚካሄዱ ሥልጠናዎች ድጋፍ ይሰጣል ፤

፭· ለተማሪዎች የደረጃ ሽግግርና ለልዩ ልዩ ምልመላ የሚያገለግሉ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጡ ፈተናዎች እንዲዘጋጁና እንዲሰጡ ያደርጋል ፣ የምስክር ወረቀቶችን ይሰጣል ፤

፮· የትምህርት መሣሪያዎችና መጽሐፍት በበቂ ጥራትና መጠን እንዲገኙ ያደርጋል ፤

፯· የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞችን ያቋቁማል ፣ ስለው ስጣዊ አስተዳደራቸው አቋም ውሣኔ ይሰጣል ፣ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች መግቢያ መመዘኛዎችን ይወስናል ፤

፰· በግል ለሚቋቋሙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች እንዲሁም በማናቸውም ደረጃ በውጭ ድርጅቶችና ባለሀብቶች ለሚቋቋሙ ትምህርት ቤቶች ሥልጣኑ በግልጽ ለሌላ አካል በሕግ ካልተሰጠ በስተቀር ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል ፤

፱· ትምህርትን በጥራት ለማስፋፋት የሚያግዙ ፕሮጀክቶችን አዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል ፣ የክልል ፕሮጀክቶችን ዝግጅትና አፈጻጸምን ያበረታታል ፣ የቴክኒክ ድጋፍም ይሰጣል ፤

፲· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለአናሳ ብሔረሰቦች ፣ ለሴቶች ፣ ለሕፃናትና ለጎልማሶች ለሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶች ልዩ ድጋፍ የሚሰጥበትን መንገድ ይቀይሳል ፤

፲፩· በየደረጃው የሚሰጠውን ትምህርት በመገናኛ ዘዴዎች ይደግፋል ፣ ክልሎች የራሳቸውን የትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ሲያቋቁሙ ይረዳል ፤

፲፪· የትምህርት መረጃዎችን ይሰበስባል ፣ ያጠናቅራል፣ ያሠራጫል፤

፲፫· ለተማሪዎች የሚሰጡ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚጠናከሩበትን ስልት ይቀይሳል ፤

፲፬· በሌሎች በፌዴራል መንግሥቱ አካላት ሥር የሚተዳደሩ የትምህርትና የማሠልጠኛ ተቋሞች የብቃት ደረጃቸውን ያሟሉ ሆነው እንዲገኙ ይቆጣጠራል፣ የብቃት ማረጋገጫም ይሰጣል ፤

፲፭· ከውጭ አገር የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ለሚሰጡ ዲግሪዎች ፣ ዲፕሎማዎችና የምስክር ወረቀቶች ደረጃ ማረጋገጫ ይሰጣል ።

3. determine the educational curriculum offered at the level of senior secondary schools, higher education institutions and training institutions of a similar status, and the type and standard of certificates to be awareded to students; provide assistance to Regional Governments in the preparation of educational curriculum for elementary and junior secondary schools; ensure that the curriculum prepared at any level is free from religious, political and cultural influences;

4. determine the qualifications required for teaching at each level of education; train teachers and educational personnel as may be necessary and provide assistance to training programmes offered at regional level;

5. cause the preparation and offering of examinations given at the national level for purposes of promoting students from one level of education to another and for various recruitments; award certificates thereto;

6. ensure the availability of educational materials and textbooks in adequate quality and quantity;

7. establish higher education institutions, determine their internal administrative organization; determine the criteria for admission to higher education institutions;

8. except insofar as such power is expressly given by law to another organ, license private higher education institutions as well as any schools established by foreign organizations and investors and supervise same;

9. prepare and implement projects designed to improve the quality and enhance the expansion of education; encourage and give technical assistance to Regions in the preparation and implementation of such projects;

10. in cooperation with the appropriate organs, devise ways and means of providing special assistance in rendering educational services to minority nationalities, women, children and adults;

11. ensure that the education given at every level is being supported by educational mass media; assist Regions in establishing their own educational mass media;

12. collect, compile and disseminate information on education;

13. devise ways and means of encouraging the provision of various student services;

14. supervise educational and training institutions run by other Federal Government organs with a view to ensuring their compliance with the prescribed standard, and accredit same;

15. classify degrees, diplomas and certificates awarded by foreign higher education institutions.

፳፪· <u>የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር</u>

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· የጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል ፤

፪· ሪፈራል ሆስፒታሎችን እና የጥናትና የምርምር ማዕከሎችን ያቋቁማል ፣ ያስተዳድራል ፤

22. The Ministry of Health

The Ministry of Health shall have the powers and duties to:

1. cause the expansion of health services;
2. establish and administer referral hospitals as well as study and research centers;

www.fag.gov.et

ፎ. የጤና አገልግሎቶች ሊኖራቸው የሚገባውን ደረጃ ይወስናል ፣ ለሆስፒታሎችና በውጭ ድርጅቶችና ባለሃ ብቶች ለሚቋቋሙ የጤና አገልግሎት ተቋሞች ሥልጣኑ በግልጽ ለሌላ አካል በሕግ ካልተሰጠ በስተቀር ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤

፬. በሕዝብ ጤና አገልግሎት በልዩ ልዩ ደረጃ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን ደረጃ ይወስናል ፣ የሙያ ችሎታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል ፤

፭. ሃገሪቱ ውስጥ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ መድኃኒቶ ችንና የህክምና መሣሪያዎችን ይመዝግባል ፣ ይቆጣ ጠራል ፤

፮. የባሕል መድኃኒቶች እንዲጠኑ ያደርጋል ለዚህም የምርምርና የሙከራ ማዕከሎችን ያደራጃል ፤

፯. ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማጥፋት የሚያ ስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል ፣ ተግባራዊነቱንም ይከታ ተላል ፤

፰. የሕዝቡን ጤና ለመጠበቅ ተገቢውን የኳራንቲን ቁጥጥር ያደርጋል ፤

፱. ምግብ ለጤና ሊውል የሚችልበትን ጥናት ያካሂዳል ።

፳፫. <u>የፍትሕ ሚኒስቴር</u>

የፍትሕ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩. የሕግ ጉዳዮችን በሚመለከት የፌዴራል መንግሥቱ ዋና አማካሪ ሆኖ ይሠራል ፤

፪. በፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር በሚወድቁ ወንጀሎች ፌዴራል መንግሥቱን በመወከል ይከራ ከራል ፤

፫. የፌዴራል የፖሊስ ኃይልንና የፌዴራል እሥር ቤት አስተዳደርን በበላይነት ይመራል ፣ ይቆጣጠራል፤

፬. በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ ያዛል፣ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን ያደርጋል ፣ በሕግ መሠረት የወንጀል ክስ ያነሳል ፤

፭. የወንጀል መነሻዎችንና የመከላከያ ዘዴዎችን ያጠናል፣ ወንጀል የሚቀንስበትን ሥልት ይቀይሳል፤

፮. የወንጀል ድርጊት ምሥክሮች እንዳስፈላጊነቱ ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል ፤

፯. በወንጀል ድርጊት ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ክስ ለመመስረትና ለመከራከር አቅም ለሌላቸው ግለሰቦች ካሣ እንዲያገኙ በፍትሐ ብሔር ክስ ይረዳል፤

፰. የሕዝቡን እንዲሁም የፌዴራል መንግሥቱን መብትና ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በፌዴ ራልና በክልል ፍርድ ቤቶች በማንኛውም ዳኝነት ሰሚ አካል ወይም የሽምግልና ጉባዔ ክስ ይመሰርታል ፣ ክስ እንዲመሠረት ያደርጋል ወይም ጣልቃ በመግባት ይከራከራል ፤

፱. ዓላማቸው ትርፍ ለማግኘት ያልሆኑ የውጭ ድርጅቶ ችንና እንቅስቃሴያቸው በአንድ ክልል ያልተወሰኑ ማሕበሮችን ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር ይመዘግባል ።

፲. ፌዴራል መንግሥቱ ወይም አካላቱ ተከራካሪ የሚሆኑ ባቸውን የፍትሐ ብሔር ክሶችንና የመብት ጥያቄዎችን አያያዝ እንደአስፈላጊነቱ ይከታተላል ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል ፣ ለዚሁም ብቃት ያለው የሰው ኃይል መመደቡን ያረጋግጣል ፤

፲፩. በፌዴራል መንግሥቱ አካላትና በክልሎች ጥያቄ ሲቀ ርብለት የሕግ ረቂቆች በማዘጋጀት ይረዳል ፤

3. determine standards to be maintained by health services; except insofar as such power is expressly given by law to another organ, issue licences to and supervise hospitals and health services established by foreign organizations and investors;
4. determine the qualifications of professionals required for engaging in public health services at various levels; issue certificates of competence to same;
5. cause the study of traditional medicines, organize research and experimental centers for same;
6. cause research to be undertaken on traditional medicines and, for this purpose, organize centers for research and experiment;
7. devise and follow up the implementation of ways and means of preventing and eradicating communicable diseases;
8. undertake the necessary quarantine controls to protect public health;
9. undertake studies with a view to determining the nutritional value of foods;

23. *The Ministry of Justice*

The Ministry of Justice shall have the powers and duties to;

1. be chief advisor to the Federal Government on matters of law;
2. represent the Federal Government in criminal cases falling under the jurisdiction of the Federal Courts;
3. as the superior authority, direct and supervise, the Federal, police force and prison administration;
4. instruct for investigation where it believes that a crime, falling under the jurisdiction of the Federal courts, has been committed; order the discontinuance of an investigation or instruct for further investigation on good cause;
5. study the causes of and the methods for prevention of crimes;
6. see to it that witnesses to a criminal case are accorded protection, as necessary;
7. assist victims of crimes in civil proceedings for the recovery of damages resulting from grave injury where such victims are unable to institute such proceedings in the Federal Courts;
8. institute, cause to be instituted or intervene in proceedings before Federal and Regional Courts; any judicial body or arbitration tribunal where the rights and interests of the public and of the Federal Government so require;
9. register, in cooperation with other concerned organs, non-profit making foreign organizations and trans-Regional associations;
10. follow-up, as necessary, the handling of civil suits and claims to which the Federal Government or its organs are a party; cause reports to be submitted to it on same, where it find it necessary, and ensure that competent manpower is assigned for the purpose;
11. assist in the preparation of draft laws when so requested by Federal Government organs and Regional Governments;

www.fag.gov.et

፲፪· በፌዴራል መንግሥት ፍርድ ቤቶች መከራከር ለሚችሉ ጠበቆች ፈቃድ ይሰጣል ፣ ይቆጣጠራል ፣ ይሠርዛል ፤

፲፫· ከሰብአዊ መብት አጠባበቅ አንፃር የሕዝብን ንቃተ ሕግ ለማዳበር በተለያዩ ዘዴዎች የሕግ ትምህርት ይሰጣል፣ የሕግ ትምህርትንና ሥልጠናን በሚመለከት ከሚመለከተው አካል ጋር ይተባበራል ፤

፲፬· የሞት ፍርድ በተፈረደበት ጉዳይ ላይ ይቅርታ እንዲ ደረግ የተጠየቀ እንደሆነ መዝገቡን ከአስተያየቱ ጋር ለርዕሰ ብሔሩ ያቀርባል ፤

፲፭· የኮዲፊኬሽንና ሕጐችን የማጠቃለል ሥራ ያካሂዳል፣ የክልሎችን ሕጐች ያሰባስበል ፣ እንደአስፈላጊነቱም እንዲጠቃለሉ ያደርጋል ።

፳፬· የማስታወቂያና የባህል ሚኒስቴር

የማስታወቂያና የባህል ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· የፌዴራል መንግሥቱ ቃል አቀባይ በመሆን ይሠራል ፤

፪· ባህል ፣ ኪነጥበብ፣ ሥነ ጥበብና የፈጠራ ችሎታ እንዲዳብርና እንዲስፋፉ ያበረታታል ፤

፫· የኢትዮጵያን ቅድመ ታሪክ፣ ታሪክና ባሕል ያጠናል ፣ ጥንታዊ ሐውልቶችና ሌሎችም ታሪካዊ ቅርሶች ተፈልገው እንዲገኙ ፣ እንዲጠበቁ ፣ እንዲጠኑ፣ እንዲታ ደሱና ጥቅም ላይ እንዲውሉ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፣ ቅርሶችንና በመጥፋት ላይ ያሉ ባህሎችን ከዝርዝር መግለጫ ጋር ይመዘግባል ፤

፬· የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋዎች እንዲጠኑ ፣ ሥነጽሑፎቻቸውም እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል ፤ ያበረታታል፤

፭· ስለቅርሶች ጥናትና እንዲሁም ቅርሶችን ለምርምርና ለኢግዚቢሽን በጊዜያዊነት ወደ ሌላ አገር ለመላክ ስለሚቻልበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፣ አፈጻጸሙንም ይቆጣጠራል ፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተ ባበር ከሌሎች አገሮች ጋር የባህል ትብብር እንዲስፋፉ ያደርጋል ፤

፮· ኢትዮጵያንና ሕዝቦችዋን ፣ እንዲሁም ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን በሃገር ውስጥና በውጭ ያስተዋውቃል፤

፯· በሃገሪቱ የፊልም ሥራና የተውኔት ጥበብ የሚዳብር በትን ሁኔታ ያመቻቻል ፤

፰· ብሔራዊ ቤተመጻሕፍት ፣ ቤተመዛግብትና አብያተ መዘክሮች እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፱· ሥርጭታቸው በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ የተወሰነ ከሆኑት ጋዜጦችና መጽሔቶች በስተቀር ለማንኛውም የፕሬስ ሥራ እንዲሁም በሀገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ የውጭ ሃገር የፕሬስ ወኪሎች ፈቃድ ይሰጣል ።

፳፭· የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· ሀገሪቱ ስላላት የውጭ ግንኙነት ጥናት በማድረግ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መመሪያ እያዘጋጀ ለመንግሥት ያቀርባል ፣ ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይከታተላል ፤

፪· ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል በሕግ ካልተሰጠ በስተቀር፣ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግሥታትና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርጋቸውን በመንግሥት የተፈቀዱ ውሎችና ኢንተርናሽናል ስምምነቶች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይፈርማል፣ እንዲሁም ውሎችና ኢንተርናሽናል ስምምነቶች እንዲ ጸድቁ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ፎርማሊቲዎች ሁሉ ያከናውናል፤

12. issue, supervise and revoke licences to advocates for practice before courts of the Federal Government;
13. provide legal education through the use of various methods with a view to raising public legal consciousness in relation with protection of human rights; cooperate with the appropriate body as regards legal education and training;
14. submit to the Head of State, together with an opinion, the record of any case involving death sentence with respect to which petition for pardon has been lodged;
15. carry out the codification and consolidation of laws; collect laws of Regional Governments and consolidate same as necessary.

24. The Ministry of Information and Culture

The Ministry of Information and Culture shall have the powers and duties to:

1. be the spokesman of the Federal Government;
2. encourage the development and expansion of culture, arts, fine arts and creative talent;
3. study Ethiopian pre-history, history and culture; make the necessary provisions for the discovery, protection, study, maintenance and utilization of ancient monuments and other historical relics; keep a register of antiquities and cultures which are in the process of extinction, together with detailed description;
4. cause, assist and encourage the study of the language of Ethiopian nations/nationalities and the enhancement and expansion of literature;
5. issue and supervise the implementation of directives concerning the study of antiquities as well as the conditions under which they may temporarily be taken to another country for purposes of research or exhibition; in cooperation with the concerned organs, promote cultural cooperation with other countries;
6. publicize, both locally and abroad, Ethiopia and its peoples as well as social and economic activities being carried out;
7. create conditions conducive to the development of the country's film production and theatrical arts;
8. cause the establishment and expansion of national libraries, archives and museums;
9. license any press activity other than newspapers and magazines the distribution of which is limited to one Region; and issue permits to foreign press correspondents stationed in the Country.

25. The Ministry of Foreign Affairs

The Ministry of foreign Affairs shall have the powers and duties to:

1. based on studies undertaken on the country's foreign relations, formulate and submit to the government policy guidelines on foreign affairs and, upon approval, follow up their implementation;
2. in consultation with the concerned organs, negotiate and sign treaties and agreements Ethiopia enters into with other states and international organizations which are approved by the Government, except insofar as such power is specifically given by law to another organ, and effect all formalities of ratification of treaties and agreements;

www.fag.gov.et

ሸ/ ሌሎች የመንግሥት አካላት ከውጭ አገር መንግሥታትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚያደርጓቸውን ግንኙነቶች ያስተባብራል፤

ቀ/ በኢትዮጵያ ከሚገኙ የውጭ አገሮች መንግሥታት እንደራሴዎች ፣ ቆንስሎችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች ጋር እንደአስፈላጊነቱ በመገናኘት የጋራ ጥቅሞች የሚጠበቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል ፤

በ/ በውጭ አገር የኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክና የቆንስላ ሚስዮኖችን እንዲሁም በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ቋሚ መልእክተኞች ጽሕፈት ቤቶችን ተግባራት ያስተባብራል፣ ሥራቸውንም ይቆጣጠራል ፤

ተ/ ሥልጣኑ በተለይ ለሌላ አካል ካልተሰጠ በስተቀር፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የፈረማቸው ውሎችና ኢንተርናሽናል ስምምነቶች የሚያስከትሏቸው መብቶችና ግዴታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል ፤

ኀ/ ኢትዮጵያ ከሌላ መንግሥትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የምታደርገውን ማናቸውም ውልና ኢንተርናሽናል ስምምነት የተመሰከረበትን ዋናውን ቅጅ መዝግቦ ይጠብቃል፤

ነ/ የኢትዮጵያ መንግሥት በብዙ መንግሥታት መካከል የሚደረጉ ስምምነቶችን አስቀማጭ በሚሆንበት ጊዜ ይህን የመሰለ ባለአደራነት የሚጠይቀውን ተግባር ያከናውናል፤

አ/ በኢንተርናሽናል ሕግና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ስምምነቶች ለውጭ ሀገር መንግሥታት እንደራሴዎችና ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወኪሎች የተሰጡ መብቶች እንዲከበሩ ያደርጋል ፤

ኘ/ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሀገሪቱ ጥቅምና መብት እንዲጠበቅና በሌሎች መንግስታት እንዲከበር እንዲሁም በውጭ ሀገር የሚገኙ የኢትዮጵያ ዜጐች መብትና ጥቅም እንዲጠበቅ ያደርጋል ፤

ኘሸ/ ከጐረቤት አገሮች ጋር ያለው መልካም ጉርብትና እንዲጠናከር ያደርጋል፤

ኘቀ/ የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ይሰጣል፤

ኘበ/ ጥገኝነትና የኢትዮጵያ ዜግነት እንዲሰጣቸው የሚጠይቁ ሰዎችን ጉዳይ በሚመለከት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር እንዲከናወን ያደርጋል ።

ፀ፮/ <u>የአገር መከላከያ ሚኒስቴር</u>

የአገር መከላከያ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖረታል፤

ፀ/ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሃገሪቱን የግዛት ሉዐላዊነት ያስከብራል ፤

ፀ/ መከላከያ ሠራዊት ያቋቁማል፣ ያስታጥቃል ፣ ይቆጣጠራል ፣ የውጊያ ብቃታቸውን ያረጋግጣል፤

ፀ/ የሃገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮች የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽኦ ያካተተ መሆኑንና ተግባሩንም ከፖለቲካ ድርጅት ወገናዊነት ነፃ በሆነ አኳኋን ማከናወኑን ያረጋግጣል፤

ፀ/ የመከላከያ ሠራዊቱን ማሠልጠኛ ተቋማት እንዲደራጁ ያደርጋል ።

ፀ/ ከክልል አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም ወይም ማናቸውም ክልል ሕገ መንገሥቱን በመጣስ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ በሕገ መንግሥቱ በተደነገገው መሠረት ሲታዘዝ ፀጥታን ያስከብራል፤

3. coordinate all relations of other government organs with foreign states and international organizations;

4. keep contacts as may be necessary, with foreign diplomatic and consular representatives in Ethiopia as well as with representatives of international organizations with a view to facilitating the protection of mutual interests;

5. coordinate and supervise the activities of Ethiopia's diplomatic and consular missions and offices of the permanent representatives of Ethiopia to international organizations;

6. ensure the enforcement of rights and obligations arising from treaties and agreements signed by the Ethiopian Government except insofar as specific power has legally been delegated to another organ;

7. register and keep all authentic copies of international treaties and agreements concluded between Ethiopia and other states or international organizations;

8. perform the functions of a depository of multilateral treaties and agreements when the Ethiopian Government is such a depository;

9. ensure the privileges and immunities of foreign diplomatic missions and representatives of international organizations under international law and treaties to which Ethiopia is a party are respected;

10. in cooperation with the appropriate organs, safeguard the interests and rights of the country and ensure that they are respected by foreign states and that the interests and the rights of Ethiopian nationals abroad are protected;

11. ensure that good neighbourly relations with neighbouring countries are strengthened;

12. issue diplomatic passports;

13. carry out, in cooperation with the appropriate organs, matters regarding persons who apply for asylum and Ethiopian nationality.

26. *The Ministry of National Defence*

The Ministry of National Defence shall have the powers and duties to:

1. in cooperation with the appropriate organs, defend the territorial integrity of the country;

2. establish, equip and supervise defence forces and ensure their combat capabilities;

3. ensure that the composition of the national defence force embodies fair representation of nations, nationalities and peoples and that it carries out its duties in a manner devoid of partiality to political parties;

4. organize training establishments of the defence forces;

5. enforce security measures where situations endangering public safety are beyond the control of Regional Governments;

www.fag.gov.et

፮· አግባብ ያላቸውን የፌዴራል መንግስትና የክልል አካላት የአገር መከላከልን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ያስተባብራል ፤ በመተባበርም ይሠራል፤

፯· ለሠራዊቱ የሚያስፈልጉትን የጦር ሠፈሮችና የመኖሪያ ሠፈሮች እየሠራና እያሠራ ያደራጃል፤

፰· በአገር ውስጥ የሚገኝ ሃብት በክተት ጊዜ በተባበረ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዘዴ እያጠና ያስወ ስናል ፤

፱· የክተት አዋጅ በሚታወጅበት ጊዜ ሕብረተሰቡ ከጠላት አደጋና ጥቃት ራሱን የሚከላከልበትን ዕቅድ ያወጣል፣ ሲወሰንም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል ፤

፲· የሠራዊቱ አባላት በሠላም ጊዜ በአገሪቱ የልማት ሥራዎች መሣተፋቸውን ያረጋግጣል ።

፳፯· ስለ ሌሎች የፌዴሬሱ አስፈጻሚ አካላት

ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆኑ ሌሎች የፌዴራል መንግሥቱ አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጐች በተደነገገው መሠረት ይሆናል ።

ክፍል አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳፰· የተሻሩና ተፈጻሚነታቸው ስለሚቀጥል ድንጋጌዎች

፩· የሚከተሉት ሕጐች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፤

ሀ· የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የማዕከልና የክልል አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፺፩/፲፱፻፹፭ (እንደተሻሻለ) የማዕከል አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር የሚመለከቱት ድንጋጌዎች ፤

ለ· የጠቅላይ ሚኒስትርንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፹፫ ።

፳፱· መብትና ግዴታዎች ስለማስተላለፍ

፩· የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የንግድ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተላልፈዋል፤

፪· የውጭ ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር ተላልፈዋል ።

፫· የተፈጥሮ ሃብት ልማትና የአካባቢ ጥበቃ ሚኒስቴር መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ፤

ሀ· ከደንና ዱር አራዊት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ለግብርና ሚኒስቴር፤

ለ· ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ለአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፤

ሐ· በ (ሀ) እና (ለ) ከተመለከቱት ውጪ ያሉት ለውሃ ሃብት ሚኒስቴር ተላልፈዋል ።

6. cooperate with and coordinate the activities of the appropriate Federal and Regional Government organs in matters relating to the defence of the country,
7. construct and cause the construction of and organize camps and facilities required by the defence forces;
8. prepare and get authorized advance plans for the coordinated utilization of resources in the country that may be required for an event of national mobilization;
9. prepare schemes whereby the population can defend itself or guard against enemy threats and attacks where general mobilization is declared; implement same, upon authorization, in cooperation with the concerned organs;
10. ensure that in time of peace the defence forces participate in the country's development activities.

27. Other federal Executive Organs.

The powers and duties of other executive organs of the Federal Government, accountable to the Council of Ministers, shall be as provided for under other relevant laws.

PART FOUR
Miscellaneous

28. Repeals and Saving

1. The following laws are hereby repealed:

a. provisions relating to the powers and duties of central executive organs, under the Definition of Powers and Duties of the Central and Regional Executive Organs of the Transitional Government of Ethiopia Proclamation No. 41/1993 (as amended).

b. The Definition of Powers and Duties of the Prime Minister and the Council of Ministers Proclamation No. 2/1991.

29. Transfer of Rights and Obligations

1. The rights and obligations of the Ministries of Industry and Trade are hereby transferred to the Ministry of Trade and Industry.
2. The rights and obligations of the Ministry of Foreign Economic Cooperation are hereby transferred to the Ministry of Economic Development and Cooperation.
3. The rights and obligations of the Ministry of Natural Resources Development and Environmental Protection are hereby transferred to:
   a. the Ministry of Agriculture, as relating directly to Forestry and Wildlife.
   b. the environmental Protection Authority, as relating direcctly to environmental protection.
   c. the Ministry of Water Resources, as relating to those outside of the ones, specified under (a) and (b) herein above.

www.fag.gov.et

፴· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከነሐሴ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

30. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 23rd day of August, 1995.

Done at Addis Ababa, this 23rd day of August, 1995

NEGASSO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE